# በ2016 በጀት ዓመት የተከናወኑ የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች የተገኙ ግኝቶች፣

የአብክመ ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራትን መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት የተከናወኑ ተግበራትን የሚገልጽ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሰረት አስቻይ ሁኔታዎችን በመጠቀም በ2016 በጀት ዓመት የተከናወኑ የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች የኦዲት ግኝቶችን የሚያሳይ የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል:-

1. የክዋኔ ኦዲት የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ተግባራት ኢኮኖሚያዊ ፣ በቅልጥፍና እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በማከናወን የተቋቋሙበትን ዓላማ ማሳካታቸውን ለማረጋገጥ የሚደረግ ኦዲት ነው፡፡
2. በ2015/16 መ/ቤታችን በክዋኔ ኦዲት ሁለት የልዩ ኦዲት ሥራዎችና 6 በመደበኛ የተጀመሩ የክዋኔ ኦዲቶችን በማጠናቀቅ ሪፖርታቸው ለየሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ አድርጓል፡፡ ሪፖርታቸው የወጡትን ከላይ የተጠቀሱትን ስድስት መደበኛ የክዋኔ ኦዲት የተከናወነባቸው ተቋማት የኦዲት ግኝቶችንና የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መነሻ በማድረግ በግኝቶቻቸው ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ መውሳዳቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት የተካሄደ ሲሆን የክትትል ኦዲቱ ከተካሄደባቸው ተቋማት መካከል በዚህ አጭር ሪፖርት ከግኝቶች ጉልህነትና ከጊዜ አንጻር ስፋቱን ለመመጠን ሲባል ለተከበረው ም/ቤት ለንባብ የቀረበው በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዩች ላይ ብቻ ሲሆን የተካተቱት ሪፖርቶችም በአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም፤ በአብክመ ሥራና ስልጠና ቢሮ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መንግሥታዊ ድጋፎች አቅርቦትና አጠቃቀም፤ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ዓ.ም በመንግስት የተወረሱና በአብክመ ከተሞችና መሰረተ ልማት ቢሮ ስር እየተዳደሩ ያሉ የቀበሌ ቤቶች አስተዳደርና አጠቃቀም እና በአማራ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ የዘር ማምረት፣ ዘር ዝግጅትና ግብይትን በተመለከተ መደበኛ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትንና በክትትል ወቅት የታዩ መሻሻሎችን ይሆናል፡፡
3. ለክዋኔ ኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዘርፎቹ እንዲመሩባቸው መንግስት ያወጣቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፤ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በህግ የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት፣ የየመ/ቤቶች የሥራ ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደአስፈላጊነቱ ከየመ/ቤቶቹ ደንበኞች/ተገልጋይች፣ ከ3ኛ ወገን የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በኦዲት ሥራው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

4. የኦዲት ሥራውም ዓለም አቀፍ እና አገራዊ የክዋኔ ኦዲት አሰራር መርሆችንና ደረጃዎችን ተከትሎ የተከናወነና እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ ሲጠናቀቅ ረቂቅ የእውነታ ማረጋገጫ (Fact sheet) ተዘጋጅቶና ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ ተካሂዶ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ ግኝቶቹም አስተማማኝና ተጨባጭ ማስረጃዎች ያሏቸው ናቸው፡፡ በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ግኝቶች በናሙና በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች ብቻ መሆኑንም ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባ እያሳሰብኩ ከዚህ በመነሳት ዋና ዋና ግኝቶችን በአጭሩ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ፤

በክልሉ በናሙና 431 ፕሮጀክቶች ተመርጠው በተካሄደው የመደበኛ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መነሻነት በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ግኝቶችን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡-

5. እየተገነቡ በሚገኙ 56 የመንግስት ፕሮጀክቶች ከተመደበላቸዉ የገንዘብ መጠን በተጨማሪ የበጀት ክለሳ (የገንዘብ ጭማሪ) ያደረጉ በመሆኑ ብር 1,111,552,451.01 ተጨማሪ ወጪ ያስከተለ መሆኑ፣
6. ቁጥራቸው 41 የሚደርሱ የመንግስት ፕሮጀክቶች ብር 1,497,280,997.96 ወጪ ከወጣባቸዉ በኋላ ግንባታቸው የተቋረጠ መሆኑ፣
7. በሚመለከተው አካል የጭማሪ በጀቱ ሳይፈቀድላቸዉ (የበጀት ክለሳ ሳይደረግ) በ13 ፕሮጀክቶች ላይ ብር 51,976,322.30 ከተፈቀደዉ የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ ተፈጽሞባቸዉ የተገኙ መሆኑ፣
8. በክልሉ ዉስጥ ብር 390,693,457.13 ወጪ የተደረገባቸዉና በአብክመ ዉሃና ኢነርጅ ቢሮ የተገነቡት 5 የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች ( ሸበል በረንታ፣ አለፋ ጣቁሳ፣ ባቲ፣ ወረኢሉ እና ስናን) ግንባታቸዉ ከ2012 ጀምሮ ቢጠናቀቅም የኦዲት ሥራዉ እስከተጠናቀቀበት ድረስ የሚፈለገዉን አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፡፡
9. በክልሉ ዉስጥ ያሉ የመንግስት ፕሮጀክቶች ባለቤት አስፈጻሚ መ/ቤቶች ወቅታዊና የተሟላ የፕሮጀክት ፕሮፋይል መረጃዎችን የያዘ ሪፖርት ለፕላንና ልማት ቢሮ የማይልኩ መሆኑና አልፎ አልፎ የሚልኩ መ/ቤቶችም ፕሮፋይሉ ሊያካትታቸዉ የሚገባዉን የፕሮጀክት መረጃዎች (ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ፣ የፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ጊዜ፣ ለፕሮጀክቱ የተመደበዉ በጀት፣ ለፕሮጀክቱ የተደረገ የበጀት ማሻሻያ/ክለሳ፣ ፕሮጀክቱ እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ የተከፈለ የገንዘብ መጠን፣ የፕሮጀክቱ ፊዚካል አፈጻጸምና የመሳሰሉትን) አሟልተዉ የማይልኩ መሆኑ፣

10. ቢሮዉ ከ2011—2015 ባሉት ዓመታት ዉስጥ በፕሮጀክቶች የሚስተዋሉ የአሰራር ስርዓት ችግሮችን የዳሰሳ ጥናት በየበጀት ዓመቱ ሊያከናውን የሚገባዉ ቢሆንም ማጥናት የቻለዉ በ2013 በጀት ዓመት ብቻ ሲሆን በቀሪዎቹ ዓመታት ምንም ዓይነት የዳሰሳ ጥናት ያላከናወነ መሆኑ፡ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ግኝቶች ነበሩ፡፡

## በክልሉ ሥራና ስልጠና ቢሮ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መንግሥታዊ ድጋፎች አቅርቦትና አጠቃቀምን በተመለከተ፤

11. በናሙና ከታዩት ቢሮዎች፣ ሁለት ዞኖችና 14 ከተሞች ከተገኙ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ግኝቶችን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡-
12. በአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ እና በአብክመ ከተሞችና መሠረተ ልማት ቢሮ በ14 ከተሞች በድምሩ ለ49 ጥቃቅና እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገብያ ትስስር ተፈጥሮላቸው እና ቅድመ ክፍያ ከአሰሪ መ/ቤቶች ወስደው በውላቸው መሰረት ሥራውን ሳያከናውኑ የቀሩና የወሰዱትን ቅድመ ክፍያ ብር 16,502,050.64 ሳይመልሱ ስራ ያቋረጡ የጥቃቅና እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው፤
13. በክልሉ ሥራና ስልጠና ቢሮ የቴክኖልጅ ድግግሞሽ ለመቆጣጠር እና ከመስክ እይታ ባለፈ ቴክኖሎጂ ያመጣውን ተጨባጭ ለዉጥ ለማረጋገጥና በተገቢው ለመገምገም የኢንደስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ውጤትና ፋይዳ ላይ የዳሰሳ ጥናት ያልተጠና መሆኑ፤
14. በናሙና በታዩት ሰሜን ሸዋና ምስራቅ ጎጃም ዞኖችና ደብረ-ብረሃንና ደብረ-ማርቆስ ከተማ አስተዳደሮች በአሰልጣኞችና በኢንስትራክተሮች ተቀድተው ለኢንተርፕራይዞች ከተሸጋገሩት ቴክኖሎጂዎች ውስጥ 54.7 በመቶ የሚሆኑት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤
15. በተጠቀሱት ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተሰጥተው ከታለመላቸው ዓላማ ውጪ የዋሉ በድምሩ 376 ሸዶች፣ ኮንቴነሮች እና የገበያ ማዕከላት መገኘታቸው፣(ተዘግተው የተቀመጡ/የጠፉ 58፣ ለሌላ ሰው የተከራዩ 241፣ ለመኖሪያ ቤት የዋሉ 36 እና ለሌላ ላልተፈቀደ አገልግሎት የዋሉ 41 መኖራቸው )፣
16. ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ሊያውሉ ሲገባ በናሙና በታዩት በምስራቅ ጎጃም እና በሰሜን ሸዋ ዞኖች 109 ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት

ዓላማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ብር 23,899,841.20 ተግባር ላይ ሳያውሉ የተገኘ መሆኑ፡፡

17. በክልሉ ውስጥ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የተዘዋዋሪ ብድር ተበድረው የወሰዱ 742 ኢንተርፕራይዞች ውል በገቡበት 5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ከተበደሩት እና መመለስ ከሞገባቸው ብር 234,437,588.50 ውስጥ ብር 81,819,044.88 (33.61%) ሳይመልሱ የተገኘ፣

## በአብክመ ከተሞችና መሰረተ ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ዓ.ም በመንግስት የተወረሱና አሁን በቢሮው ስር እየተዳደሩ ያሉ የቀበሌ ቤቶችን አስተዳደርና አጠቃቀም በተመለከተ፤

18. "በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ዓ.ም በመንግስት የተወረሱ ቤቶች አስተዳደርና አጠቃቀምን" በተመለከተ በአብክመ ከተሞችና መሰረተ ልማት ቢሮና በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ከተገኙ የኦዲት ግኝቶች በቀጣይ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ግኝቶች ዋና ዋናዎቹ፡-

19. ለኦዲት በተመረጡት በሦስቱ ከተማ አስተዳደሮች (ጎንደር፣ ደብረ ብርሃን እና ደብረ ማርቆስ ከተሞች) በቤቶች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ስር በኦዲት ወቅት በማስረጃ ከተሰበሰቡት 12,531 የቀበሌ ቤቶች መካከል 640 የቀበሌ ቤቶች ለመኖሪያነት ውል የተወሰደባቸው ቢሆንም ከውል ውጪ ለንግድ አገልግሎት እየተጠቀሙባቸው የሚገኙ ሲሆን ይህም ኦዲቱ በተከናወነበት ወቅት በተደረገ ወቅታዊ የኪራይ የዋጋ ጥናት ግምት መሰረት ቢከራዩ በዓመት ብር 12,535,200 ለመንግስት ተጨማሪ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ መሆናቸው፤

20. የተወረሱ ንብረቶችን ለማስመለስ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይርጋ ለማገድ የወጣው አዋጅ 572/2000 ዓ.ም በተቀመጠው አግባብ የይርጋ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን አቤቱታዎች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ማከራከር የማይገባቸው ቢሆንም 227 የቀበሌ ቤቶች በክስ ክርክር ላይ ያሉና 12 የሚሆኑት በፍርድ ቤት ውሳኔ ለግለሰቦች ተላልፈው የተገኙ መሆናቸው በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በመደበኛ ኦዲት ወቅት ፍርድ ቤቶች እንዳያከራክሩና የተላለፉ ቤቶችም የሚመለሱበት የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲደረግ አስተያት የተሰጠ እና ከዚህ በተጨማሪም የኢፌድሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት በቁጥር ፌደም/አፈ/5/1039 በቀን 5/02/2016 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ከመስከረም 2016 ዓ.ም

ጀምሮ ፍርድ ቤቶች እነዚህን ቤቶች የማከራከር ስልጣን እንደሌላቸው ውሳኔ ያሳለፈ ቢሆንም በክልሉ ወደ ተግባር መግባት አለመቻሉና በተገኙት ግኝቶች ላይም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

21. በናሙና በታዩት ሦስቱ ከተሞች ካርታ ያልተዘጋጀላቸው 2672 የቀበሌ ቤቶች መኖራቸው፣
22. የቀበሌ ቤቶች በየበጀት ዓመቱ የኪራይ ውል ዕድሳት ሊደረግላቸው እንደሚገባ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት በሶስቱ ከተሞች 1936 ቤቶች ዕድሳት ተደርጎላቸው የተገኘ ቢሆንም 1971 የሚሆኑ የቀበሌ ቤቶች አሁንም ዕድሳት ያልተደረገላቸው መሆኑ፤ በናሙና ከተመረጡት ከተሞች በተጨማሪ በክልሉ ባሉ ከተሞችና ዞኖች ያሉ 20,005 የቀበሌ ቤቶች ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ የውል እድሳት ሳይደረግላቸው የተገኙ መሆኑ፣
23. በቢሮው፣በከተሞች፣በክፍለ ከተሞችና በቀበሌ አስተዳደሮች መካከል ያለዉ የቤቶች ቁጥር መረጃ ከፍተኛ ልዩነት ያለ በመሆኑ  የቀበሌ ቤቶች ላልተገባ ጥቅም እንዳይውሉ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለማሳያም በአማራ ክልል ከተሞች መሰረተ ልማት ቢሮ የተመዘገበ የቀበሌ ቤቶች ብዛት 15,469 ሲሆኑ በሦስቱ ከተሞች የከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን መምሪያዎች የተመዘገበ ማስረጃ 22,800 ቤቶች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከክልሉ በ 7,331 በመብለጥ የታየ ሲሆን  በተዋረድ ከታች ባሉ  በከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደር  ቡድን (ጽ/ቤት/ክፍለ ከተሞች) የተመዘገበ የቤቶች  ብዛት ማስረጃ ደግሞ 12,531 በመሆኑ በመምሪያዎቹ ከተያዘው በ10,269  አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከፍተኛ የቁጥር ልዩነት ያለው የቀበሌ ቤቶች የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ያልተሟላ፣በዘመናዊ መንገድ ያልተደራጀና የቀበሌ ቤቶችን በግልፅ ለመለየትና ለማወቅ የማያስችል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
24. ሌላው በክልሉ የሚገኙ የቀበሌ ቤቶችን በተሟላ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚያግዝ መመሪያ አለመኖር፡፡ (በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ አዲስ መመሪያ ቢኖርም  ሳይጸድቅ  የቆየ መሆኑ)

## በአማራ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ የዘር ማምረት፣ ዘርዝግጅትና ግብይትን በተመለከተ

25. የአብክመ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ ከ2011 እስከ 2015 ዓ.ም  በዘር ማምረት፣ ዘር ዝግጅትና ግብይት ላይ የነበረውን እንቅስቃሴ በተመለከተ በተካሄደው የክዋኔ ኦዲት በተገኙ ግኝቶች መነሻነት ኢንተርፕራይዙ የወሰደው የማስተካከያ እርምጃ  ላይ የክትትል ኦዲት ሲደረግ በአጠቃላይ በ47(57.3%) በሚሆኑ ግኝቶች ላይ ሙሉ በሙሉ እና በከፊል እርምጃ ሲወሰድ በቀሪዎቹ 35 (42.7 %) በሚሆኑ ግኝቶች ላይ ደግሞ ምንም

ዓይነት የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡ በቀጣይ ትኩረትና የማስተካከያ እርምጃ ከሚያስፈልጋቸው ግኝቶች ዋና ዋና ዎቹን ለመጥቀስ፡

26. ከ2011-2016 ባሉት ስድስት በጀት አመታት የአብክመ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ የተለያዩ የሰብል ዘሮችን እንደየ ስነ-ምህዳሩ ከተጠቃሚ አርሶ አደሮች፣የግል ዘር አባዥ ድርጅቶች ዩኒየኖች፣መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ላይ ለዘር የሚፈለጉ የሰብል ዝርያዎች የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ሳይሰራ የቆየ መሆኑ የኦዲት ግኝቱ ያሳያል፡፡

27. ኢንተርፕራይዙ የአትክልትና ፍራፍሬ ፣የተለያዩ የእንስሳት መኖና የችግኝ ዘሮችን በጣቢያዎች በማምረት የአሰራር ክፍተት ለማስተካከል የሚያስችል ዘላቂ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ ዘሮች ቢመረቱም ገበያ /ፈላጊ/ የላቸውም በሚል የማያመርት መሆኑ፡፡ በሌላ በኩል በናሙና ከታዩት ሰነዶች መረዳት እንደተቻለው በ2013 በጀት ዓመት የአብክመ እንስሳት ሃብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ለእንስሳት መኖ ዘር አገልግሎት የሚውል የተለያዩ 11 አይነት ብዛቱ 472.2 ኩንታል የመኖ ዘሮች ለመግዛት ኢንተርፕራይዙን በደብዳቤ ቢጠይቅም የመኖ ዘር ያልተመረተ /የማይመረት/ መሆኑን በመጥቀስ ምላሽ ተሰጧቸው ተገኝቷል፡፡

28. በደብረ-ብርሃን፣እንጅባራ፣ቻግኒ ጣቢያዎች ላይ የዘር ጥራት ቁጥጥር ፍተሻ ላብራቶሪ ሳይቋቋም በመቅረቱ ለዘር አባዥዎች የዘር ጥራት ምርመራ አገልግሎት የማይሰጥ እና በእይታ ብቻ ዘሩ እየታየ የሚሰበሰብ መሆኑ፤

29. በቻግኒ ዘር ብዜት ጣቢያ ለመስኖ አገልግሎት የሚውል 100 ሊትር በሴኮንድ የማፍሰስ መጠን (ዲስቻርጅ-ሬት) የላቸው ዋጋቸው ብር 2,576,622.6 የሆነ አራት የውሃ ፓምፕ ጀኔሬተሮች ከግብርና በድጋፍ የተገኙ ቢሆንም ከ2012 በጀት ዓመት ጀምሮ ወደስራ ያልገቡ መሆኑ፤

30. በ2013 በጀት ዓመት ከኢንተርፕራይዙ ውጭ ለግል ድርጅት የብጠራ አገልግሎት ሲሰጥ ለብጠራ የገባ ያልተበጠረ በቆሎ ዘር ብዛት 6,283.14 ኩንታል የተበጠረ ንጹህ ዘር 6,132.88 ኩንታል ብጣሪ 199.52 ኩንታል በድምሩ 6,332.40 ኩ/ል የወጣ በመሆኑ በልዩነት 49.26 ኩንታል በብልጫ ከኢንተርፕራይዙ መጋዘን ወጥቶ ተገኝቷል

31. ከ2011 እስከ 2015 በጀት ዓመት ኢንተርፕራይዙ በኮንትራት ዘር እያባዛ ቢሆንም በየአመቱ ምርጥ ዘር አምርተው ለኢንተርፕራይዙ ያላስረከቡ አባዥዎች መረጃ ተጠይቆ ኢንተርፕራይዙ መረጃ ያልያዘና በውላቸው መሰረት ዘር ያላስረከቡ አባዥዎች ላይ ጠቅላላ ይመረታል ተብሎ ከተገመተው ዘር ዋጋ ላይ 10% ቅጣት ማስከፈል ሲገባው ሳያስከፍል መገኘቱ፡፡

32. ከ2011 እስከ 2015 በጀት ዓመት ባሉት ዓመታት ለዘር ማምረት የተመረጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከተባዮች ነፃ ስለመሆናቸው ከኳራንታይን ባለስልጣን የድጋፍ ደብዳቤ/ማስረጃ እንዲያቀርቡ የማይደረግ ሆኖ መገኘቱ ፡፡
33. በ2013/2014 ምርት ዘመን በሰሜን ሸዋ ዞን ሞረትና ጅሩ ወረዳ ኩሳዬ፣ገርባና ማንጉዶ ቀበሌዎች 16 ምርጥ ዘር አባዥ አርሶ አደሮች በኳራንታይን ባለስልጣን ይሰበሰባል ተብሎ የተገመተዉ የምርት መጠን 522.24 ኩንታል ሆኖ እያለ የተሰበሰበው 1,171 ኩንታል ሲሆን ከተገመተው በላይ ከአባዥዎች የኳራንታይን ባለስልጣን ይሁንታ ያላገኘ 648.76 ኩንታል የስንዴ ዘር ኢንተርፕራይዙ ተረክቦ መገኘቱ፤
34. በምርት ዘመኑ የተመረቱ የተለያዩ ዘር እና የከረሙ ምርጥ ዘሮች የአሰራር ስርዓቱ በማይፈቅድ ሁኔታ በአንድ መጋዝን ተከማችተው የተገኙ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የማሻሻያ አስተያየት፤

በቀረቡት የኦዲት ሪፖርቶች ከተስተዋሉ ግኝቶች ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሌሎች ሀብቶችን አመራር (management) እና የተግባራትን ኢኮኖሚያዊነት፣ ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ለማጠናከር የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶችን እናቀርባለን፣

35. በኦዲት ስራው ከተስተዋሉ ግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአንዳንድ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተከሰተ ሲሆን ይህም የመንግስት ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ እየተዳረገ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡ የአጥፊዎችም ተጠያቂነት ሊጠናከር ይገባል፡፡
36. በገቢ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የሚፈጥሩ አሠራሮችን እየፈተሹ የአሰራር ሥርአት በመዘርጋት ማምከን እንዲሁም የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ መሰብሰብ እንዲቻል ማድረግ እና የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ማስፈን ያስፈልጋል፡፡
37. በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግ እና ተጠያቂነትን ማስፈን ያስፈልጋል፡፡
38. በበርካታ መ/ቤቶች ተሰብሳቢ ሂሳቡ መቸ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩን የሚያሳውቅ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር እየተዘጋጀ ባለመሆኑ ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ

ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ሊያጠናክሩ ይገባል፡፡

39. በአንዳንድ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጐ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ የሚገባ ሲሆን ይህን ተግባራዊ በማያደርጉ የተቋማት ሃላፊዎችና ሰራተኞች ላይ ስራን ባልተመቸ ሁኔታ መምራትና ለብክነት በር በመክፈት ድርጊት ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል፡፡

40. በክልሉ የተሰበሳቢና እና ተከፋይ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣበት ሁኔታ በመኖሩ በተሰብሳቢ እና በተከፋይ ሂሳብ ላይ መወራረድ የሚችሉት እንዲወራረዱ፣ መወራረድ የማይችሉት ደግሞ በስራ ላይ ባለው ከመዝገብ የመሰረዝ መመሪያ መሰረት ምክንያቱን በማጣራት ማስረጃ በመያዝ መፍትሄ የሚያገኝበትን መንገድ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሰራ ይገባል፡፡

41. የቀበሌ ቤቶችን በሚመለከት ውላቸው በየዓመቱ ሊታደስ እና ካርታ ሊዘጋጅላቸው የሚገባ ሲሆን የቤቶችን ቁጥር በሚመለከት በየደረጃው ባሉ አካላት ተናባቢ እና ትክክለኛ መረጃ ሊኖር ይገባል፡፡ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስመለስ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይርጋ ለማገድ የወጣውን አዋጅ እና የፌዲሬሽን ም/ቤት ያስተላለፈውን ውሳኔ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ከፍርድ ቤቶች ጋር ተናቦ መሥራት የሚጠይቅ ሲሆን ባጠቃላይ የቀበሌ ቤቶችን አስተዳደርና አጠቃቀም በሚመለከት ክፍተቶችን የሚሞላ የቀበሌ ቤቶች አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ በማዘጋጀት ጠንካራ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

42. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላቱ አጠቃቀም ለኢንተርፕራይዞች ከተቀመጠላቸው የቆይታ ጊዜ ጣሪያ በላይ እንዳይበልጥ፣ ለኢንተርፕራይዞች የተሰጡ ሸዶች፣ ኮንቴነሮች እና የገበያ ማዕከልች ለታለመላቸው አላማ ብቻ እንዲውሉ፣ ለሌሎች ኢንተፕራዞች ሊውል የሚገባዉን ገንዘብ ሳያስመልሱ ቀርቶ በጥቂቶች እጅ እንዳይቀር እና በብድር አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዲይፈጥር እንዲሁም ለኢንተርፕራይዞች የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ አገልግሎት እንዲሰጡ ቢሮው እና በተዋረድ ያሉ የሥራና ስልጠና መምሪያዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተጠናከረ ድጋፍ እና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

43. የምርጥ ዘር ማምረት፣ ዘር ዝግጅትና ግብይትን በተመለከተ እቅድና ጥናት ላይ በመመርኮዝ ፍላጎትንና አዋጭነትን ማዕከል ያደረገ በቂ እና ጥራት ያለው ምርጥ ዘር በተመጣጣኝ ዋጋ በወቅቱ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ በማድግ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዙ ክልሉ የጣለበትን ዘላቂ ልማትና ዕድገት የማረጋገጥ ድርሻ በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡

44. የአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ የሚከታተላቸው ፕሮጀክቶች አስቀድሞ የተያዘው በጀትም ሆነ የትግበራ ፕሮግራም የክለሳ ጥያቄ የሚስተናገድበት እና የሚፈቀድበት ጠንካራ የአዋጭነት ግምገማ ሥርዓትን በመዘርጋት ገቢራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከአብክመ ገንዘብ ቢሮ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከርና የመረጃ ልውውጥን በማዘመን የፕሮጀክቶች አፈጻጸም እያስከተለ ያለውን የሀብት ብክነት የሚቀንስበትን መንገድ ማመቻቸት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

45. የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራን በሚመለከት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እየወሰዱት ያለው እርምጃ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡ እና እርምጃ በማይወስዱ እንዲሁም በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ላይ በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶችና እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የተጠያቂነትን ስርዓት ሊዘረጉና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

46. ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤቱን እየገጠሙት ካሉት ችግሮች አንጻር ምላሽ የሚሻ ጉዳይ በሚመለከት ማህበረሰቡ ስለ ኦዲት ሙያ ግንዛቤ በመያዙ የጥቆማ ተሳትፎው በመጨመሩ እና ለፍትሃዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሲባል በየደረጃው ካሉ የፍትህ አካላት ትእዛዝ እና ጥያቄዎች በስፋት እየቀረቡ በመሆናቸው የልዩ ኦዲት ከዓመት ዓመት በስፋት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ይህም የመደበኛ ስራውን ሊያስቀም በሚችል ደረጃ ጫና እያስከተለ በመምጣቱ ራሱን በቻለ ዳይሬክቶሬት መምራት ይቻል ዘንድ እና በሌሎችም የኦዲት ዘርፎች የኦዲት ሽፋንን ለማሳደግ መ/ቤታችን አጥንቶ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀረበው ተቋማዊ አደረጃጀት ጥያቄ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ምላሽ እንዲያገኝ ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡

47. በመጨረሻም የተከበሩ ፕሬዚዳንት፣ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የመንግስት ወጭ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና ሌሎች ኮሚቴዎች፣ የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እንዲሁም የመ/ቤቱ ሠራተኞች በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት

ታታሪነት እና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቱን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡

አመስግናለሁ!!

አማረ ብርሃኑ /ዶ/ር /

ዋና ኦዲተር

ህዳር 2017 ዓ.ም

ባህርዳር